BAY AREA
AIR QUALITY
MANAGEMENT
DISTRICT

# <u>የሕዝብ ማስታወቂያ</u>

**ነሐሴ 11 ቀን 2015 ዓ.ም**

ለ: በሚከተሉት ትምህርት ቤቶች ልጆቻቸውን ላስመዘገቡ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች:

**የሰሜን ኦክላንድ ኮሚዩኒቲ ቻርተር ትምህርት ቤት (North Oakland Community Charter School)**

**እና ያትስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Anna Yates Elementary School)**

ከዚህ በታች በተጠቀሰው የአየር ብክለት አዲሱ ወይም የተሻሻለው ምንጭ 1000 ጫማ ርቀት ውስጥ የሚገኝ ሁሉም የመኖሪያ እና የንገድ አጐራባቾች።

ከ: የቤይ አካባቢ የአየር ጥራት አመራር ዲስትሪክት

ጉዳዩ: ለሚከተሉት የአየር ብክለት ምንጮች የቀረበ የፍቃድ ማመልከቻ ቁጥር 27059:

**Sub-Slab Depressurization System**
**1001 42nd Street LLC**
**1001 42nd Street**
**Oakland, CA 94608**

---

የቤይ አካባቢ የአየር ጥራት አመራር ዲስትሪክት (“ዲስትሪክት”) እንደ ፋብሪካዎች፣ የኢንዱስትሪ ሳይቶች እና የነዳጅ ማደያዎች የመሳሰሉ ቋሚ የአየር ብክለት ምንጮች የሚቆጣጠር ተቋም ወይም ኤጀንሲ ነው፡፡

በትምህርት ቤት አካባቢ በ1000 ጫማ ርቀት ላይ አዲስ መርዛማ የአየር በካዮች አዲስ ወይም የተሻሻለ ምንጭ ለመከፈት የፍቃድ ማመልከቻ በምንቀበልበት ጊዜ እኛ ስለጉዳዩ ለሕዝብ እንድናስተዋውቅ የግዛቱ ሕግ ያስገድዳል፡፡ ይህንን ሕግ ለማክበር እኛ ሕዝባዊ ማስታወቂያ በ1/4 ማይል ርቀት ላይ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለተመዘገቡ ልጆች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች እና ከታሰበው የብክለት ምንጭ 1000 ጫማ ርቀት ውስጥ ለሚገኙ ነዋሪዎች እና የንግድ ቤቶች በሙሉ የሕዝብ ማስታወቂያ እናሰራጫለን ወይም በደብዳቤ እንልካለን፡፡

እርስዎ ይህ የሕዝብ ማስታወቂያ የደረስዎት ከላይ የተጠቀሰው የአየር ብክለት ምንጭ በተመለከተ ለዲስትሪክቱ የፍቃድ ማመልከቻ በመቅረቡ ምክንያት ነው፡፡ የታሰብ ፕሮጀክት ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡***1001 42nd Street LLC*** በመወከል አኳ ሳይንስ ኢንጂነርስ ኢንክ አሁን ያለው የብክለት ችግር ለማስተካከል በስላብ ውስጥ የሚቀበር የማስተንፈሻ ወይም የጭስ ማውጫ ስርዓት በዚህ ሳይት ለመገንባት እና ስራውን ለመስራት በማሰብ ለባለስልጣኑ አመልክቷል፡፡ ደረቅ የቆሻሻ ማስወገጃ ፈሳሽ (ፐርክሎሮኢትሊን) በዚህ አካባቢ ባለው አፈር ውስጥ መኖሩ ታውቋል፡፡

***1001 42nd Street LLC*** ይህንን የደረቅ ማጽጃ ፈሳሽ እንፋሎትን ከዚህ አካባቢ ከሚቆፈሩ ጉድጓዶች ለማውጣት ስርዓት ወይም ሲስተም በመገንበት አቅዷል፡፡ የወጣው እንፋሎት በአግባቡ ካርበን አድዞርፌሽን በተባለ ዘዴ በአግባቡ የማከም ስራ የሚደረግለት ሲሆን ከዚህ ምንጭ የሚወጣው ጭስ በአግባቡ ቁጥጥር ስር ይውላል፡፡

*የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ*

ዲስትሪክቱ የተባለውን ፕሮጀክት የፈቃድ ማመልከቻ መርምሮ ፕሮጀክቱ ከመርዛማ አየር በካዮች ልቀት ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ የጤና ጉዳቶችን ጨምሮ የዲስትሪክቱን፣ የግዛቱን እና የፌዴራል አየር ጥራት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ተፈፃሚነት ወይም አግባብነት ያላቸው መመሪያዎች ያሟላ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

*ተጨማሪ መረጃ*

ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ከፈለጉ ለዲስትሪክቱ በዚህ ማስታወቂያ መጨረሻ ላይ ባለው ስልክ ቁጥር በመደወል የዲስትሪክቱን የምርመራ ሪፖርት ኮፒዎች መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ይህንን መረጃ በዲስትሪክቱ ድህረ ገጽ፡

http://www.baaqmd.gov/permits/public-notices ማግኘት ይችላሉ

*የህዝብ አስተያየት መስጫ ጊዜ*

**ህብረተሰቡ ለዚህ እቅድ ወይም ፕሮፖዛል አስተያየት ወይም ግብረ መልስ ለመስጠት 30 ቀናት ተሰጥቷል፡፡ በታቀደው ፕሮጀክት ላይ አስተየየት መስጠት ከፈለጉ በጽሑፍ ወይም በኢሜይል አስተያየትዎን መስጠት ይችላሉ፡፡ በአማራጭነት ስልክ ደውለው ርዝመቱ እስከ 1 ደቂቃ የሚደርስ የስልክ መልዕክት መተው ይችላሉ፡፡ የዲስትሪክቱ የሰራተኛ አባል ለመልዕክትዎ ምላሽ መስጠት እንዲችል እባክዎን ስምዎን እና ስልክ ቁጥር ይተውልን።**

በታቀደው ፕሮጀክት ላይ አስተያየት መስጠት ከፈለጉ እባክዎን የሚከተሉትን የግንኙነት መረጃዎች ይጠቀሙ፡

የደብዳቤ መላኪያ አድራሻ: 1001 42nd Street LLC (AN# 27059)
Public Notice Response
BAAQMD
Engineering Division
939 Ellis Street
San Francisco, CA 94109
Attn: Flora Chan

የኢሜይል አድራሻ: fchan@baaqmd.gov

ስልክ ቁጥር: (415) 749-5122, ሣ.ቁ 5

የዚህ ፕሮጀክት የህዝብ አስተያየት መስጫ ጊዜ መስከረም 11 ቀን 2015 ዓ.ም ይሆናል፡፡